


# ድር ቢያብር አንበሳ ያስር !

## ከኢትዮጵያ ከረንት አፌርስ ዲስከሽን ፎረም በግንቦት 7 እና 8 ስለሚደረገው ዓለም ዓቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ

## ለፖለቲካና ለሲቪክ ማኅበራት የተላለፈ ሕዝባዊ ጥሪ ።

ሚያዚያ 25 ቀን 1998 ዓ.ም

ሃገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ በታሪኳ አይታውም ሆነ አጋጥሟት በማታቀው ህልውናዋን ባስደፈሩ ፣ ክብርሯን በገሰሱ፤ ኢትዮጵያዊነት ስሜቱን ፣ ኅዝባዊ ፍቅሩን ፣ በተሰለቡ የጎጠኞች አንባገነናዊ ቡድን እጅ ላይ መውደቋ የሚታወቅ ነው። ይህ በመሆኑ ሕዝባችን ለአንዴም ለሁሌም ከጨቋኞች ለመላቀቅ መንቀሳቀስ ከጀመረ በርካታ ዓመታትን አስቆጥሯል። በተለይ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. በይፋ ያስመሰከረበት ፤ ለጎጠኞች አልገዛም ባይነቱን ፤ መምረጥ የሚገባው ወገን በምርጫው ካርዱ የወያኔን ዘመነ ስልጣን እዳበቃ ያሳየበት እለት መሆኑ የማይታበል ነው ።

ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ታሪክ ታላቅ ቦታ የሚሰጠው እለት ፤ እነሆ ! አንደኛ ዓመቱን ሊያስቆጥር ጥቂት ቀናት ቀርተውታል። ታዲያንን ይህንን በተለይ ከግንቦት 8 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ  የመንቀሳቀስበ  መብቱ ባንባገነኑ መለስ ዜናዊ የተነጠቀበት እለት ጭምር ፤ በሃገር ቤት የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ብሶቱን እንዳይገልጽ ፤ መብቱ ታፍኖ የሚገኝበት ወቅት ላይ በመሆኑ፤ይህንን ከምን ጊዜውም በላይ ትግሉን አስተባብሮ የተንቀሳቀሰበትን ዕለት ፤ ለበለጠ ትግል የሚነሳበትና ለወሳኙ ትግል ጥሪ የሚያስተላልፍብት እለት ቢሆን ምንኛ በታደለ ነበር።

ይህንን እለት እኛ በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ላለፉት ከ11ወራት በላይ የሕዝባችንን ትግል በማገዙ ሂደት ላይ የተጫወትነው ሚና የማይናቅ እደሆነ ሁሉ፤ ለመጪውም የትግል ወቅት ታላቅ ሕዝባዊ ጥሪአችንን የምናስተላልፍበት ፤ የሕዝባችንን

የድረሱልኝ ጥሪውን የምናስተጋባበት እለት ሆኖ ለማሳለፍ ፤ በመላው ዓለም የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ስር ነቀል የሆነ ትእይንተ ህዝብ በማድረግ ፤ በያለንበት ሃገራት መንግስታት ፤ የህዝባችንን ብሶት በማስማት መሰረታዊ ጥያቄዎቹን በማስተላለፍ ለበለጠ ተግባራዊነት የምንነሳበት እለት እንዲሆን መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

በመሆኑም በመላው ዓለም የምንገኘውን የኢትዮጵያውያን  ለተግባራዊ እንቅስቃሴ በማደራጅቱና በማስተባበሩ በኩል ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ኅብረትና  ፣ የሲቪክ  ማኅበራት በጋራ በመሆን ያደረጓቸው እንቅስቃሴዎች ፤ በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ ባገኘናቸው ድሎች አስመስክረዋል ። ይህ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የጎለበተውን ያክል የተለያዩ ድክመቶችም እንዳልታጡበት እሙን ነው ። ይህን ስንል ፤ በተለይ በዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ስረአት አደረጃጀት አንድ ውጥ የሆን የጋራ የተግባር ግንባሩን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ አለመመስረቱ ለተለያዩ ድክመቶች መንስኤ መሆኑ እሙን ነው ። በመሆኑም በጋራ ፣ ለጋር ተግባራት የመንቀሳቀሱ ሂደት ላይ እነስተኛም ቢሆን ፤ችግር መፍጠሩ አሌ የማይባል ሃቅ ነው ።

ይህንን ለማለት ያነሳሳን ከላይ ለጠቀስንው ህዝባችን ከምን ጊዜውም በላይ ለመብቱና ለነፃነቱ የተንቀሳቀሰበትን እለት ምክንያት በማድረግ ለሚደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በአሜሪካ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን የግንቦቱን ሕዝባዊ የትግል ቀን በምን መልክና በየትኛው ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግን በተመለከተ አንድ የጋራ ከሆን ውሳኔ ላይ አለመድረሱ ያሳዘነን በመሆኑ ነው ።  በተለይ  የብዙሃን ድርጅቶች ( የሲቪክ ማኅባራት ) ለፖለቲካ ድርጅቶች አጋዥ ከመሆን ባሻገር ፤ መሠረታዊ በሆኑ ህዝባዊ እንቅስቃሴያት ላይ የመወሰኑም ብሎም የህዝብን ትግል  ወደፊለጉት አቅጣጫ ለመዘወርና  ለመከፋፍል ምክናይት ሊሆን ባልተገባቸው ነበር ። ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤው በግንባር ቀደም ደረጃ ትግሉን በመምራት ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች የጠነከር የጋራ ግንባር ባለመመሥረቱ ነው ብንል የተሳሳትን አይመስለንም ።

በመሆኑም በአፋጣኝ የፖለቲካም ሆኑ የብዙሃን ድርጅቶች ( የሲቪክ ማኅበራትን ) ለጸረ-ወያኔ ትግል በጋራ መነሳቱ ሌላ አማራጭ የማይገኝለት የወቅቱ የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የግድ እደሚል ተረድተው ዓለም አቀፍ ጠንካራ አንድነት መመስርቱ ተገቢ ነው የምንለው ።

እኛ በተለይ በመላው ክፍለ ዓለም ተበትነን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በፈጠረልን የድረ ልሳን ( Paltalk ) አማካኝነት በመቀራረብ በሃገራችን ጉዳይ ላይ በውጪ ለምናደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማስተባበሩና ፖለቲካዊ ውይይቶችና ጠቃሚ ውሳኔዎች ላይ በመድረስ የምናደርገው ለትግሉ የአጋዥነት ባህሪው ፤ ሚዛን መድፋቱን ከጀመረ ቆየት ብሏል ።

…3

በመሆኑም ይህንን በአሜሪካ የሚገኙ ወገኖቻችን እለተ ግንቦትን አስመልክቶ የተፈ-ጠረው ልዩነት ቀጣይነት ያለው ችግር ከመፍጠሩ በፊት ፤ በአጮ መቀጮት አለበት ብለን ስለምናምን ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጠቋሚ ሃሳባት ስናመላክት ፤ ከማንኛውም ፖለቲካም ሆነ ሕዝባዊ ድርጅቶች ተጸኖ ነፃ በሆነ ሃገር ፍቅር ስሜት ነው ።

1ኛ. የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ የመጀመሪያ በሆነ ሁኔታ  መብቱን ተጠቅሞ የሚበጀውን ድርጅት የመረጠበትንና በስልጣን ላይ ባላው የጎጠኞች ቡድን የተነጠቀውን ድምፁን ለማስመለስ ፤ ከምንጊዜውም በላይ መንቀሳቀስ የጀመረበትን እለት ምክንያት በማድረግ ፤ በመላው ዓለም የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በያለንበት ሃገረት በነቂስ በመውጣት ለመንግስታቱና ለኅብረተሰቡ የህዝባችንን ብሶትና የወያኔን እንባገነንነት ማጋለጠ ።

2ኛ. ይህንን ቀን በተለይ ጥያቄአችንን ብናሰማ ለትግሉና ለሕዝባችንም ጠቀሜታ እንዲኖረው በአውሮፓ የአውሮፓ ፓርላሜንት በኢትዮጵያ ጉዳይ የሚመክሩበት እለተ ማለትም ግንቦት 7 ቀን 1998 ዓ.ም ( 15. May 2006 ) መሆኑ ተግቢ ሲሆን ፤ በአኳያውም በአሜሪካ፣ የአሜሪካ ኮንገረስ ሥራውን በሚጀምርበት እለትና የሕዝባችንን መልእክት በቀጥታ ለማስተላለፍ ይበጅ ዘንድ በግንቦት 8 ቀን 1998 ዓ.ም (16 May 2006 ) ጠቃሚነቱ የማያከራክር  በመሆኑ ፤ ይህንን እለት መላው ለሕዝብ ቀመናል ፣ ለወገናችን በጋራ ለመታገል ቃል ገብተናል የሚል ጸረ-ወያኔ ሃይላት በሙሉ በጋራ በመውጣት ፤ ብሶተ - ሕዝብን ለማስማት በአንድነት እንድንቀሳቀስ በኢትዮጵያዊነታችን ጥሪአችንን እናስተላልፋለን ።

3ኛ. ይህንን እለት በሚመለከት ቀደም ብለው የወሰኑ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ማኅበራት በጋራ ማድረጉ ውጤቱ አመርቂ መሆኑን በመገንዘብ ፤ በመግባባትና በኅብረተሰቡ መካከል ልዩነት እዳይፈጠር በማሰብ ለተግባራዊነቱ እንዲንቀሳቀሱ እንጠይቃለን ።

4ኛ. በአሁኑ ወቅት በውጪም ሆነ በሃገር ቤት ያለውን ሰላማዊ ህዝባዊ ትግል በመምራት ላይ የሚገኙት ድርጅቶች ማለትም ቅንጅትም ሆነ ኅብረቱ የብዙሃን ድርጅቶች ሊጫወቱ ከሚገባቸው ሚና በላይ በመሄድ የህዝባችንን የትግል አቅጣጫ እዳያስለውጡት የፖለቲካ ድርጅታዊ ሚናቸውን በሚገባ መወጣት ያስፈልጋል በማለት መልእክታችንን እናስተላልፋለን ።

5ኛ. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እዲሉ ነውና ፤ የወቅቱ የሕዝባችን ትግልም ሆነ ዓለም አቀፉ ሁኔታዎች የግድ እያሉን ያለው ፤ በመተባበርና በጋራ በመሆን በምናደርገው ትግል ሕዝባችንን ወደሚፈልገው አቅጣጫና ውጤት በአፋጣኝ ሊያመጣው ስለሚችል፤ ቅንጅት ፣ ኅብርትና ለትግሉ አጋዥ የሆኑት   የብዙሓን ድርጅቶች (የሲቪክ ማኅበራት ) ከምን ጊዜውም በጠነከረ መልኩ ዓለም አቀፍ የሆነ ኅብርት እዲፈትሩ እንጠይቃለን ።

6ኛ. ይህንን ቀን በማንተራስና አጋጣሚውን በመጠቀም የፖለቲካም ሆን የብዙሃን ድርጅቶች በጸረ ወያኔ አቋማቸው የሕዝብን ትግል በማስተባበርና በመምራት በአንድነት መሰለፋቸውን የሚገልጽ የጋራ መግለጫ እንዲያወጡ እንጠይቃለን ።

ለማጠቃለል ፤ በመሰረቱ የፖለቲካም ሆነ የብዙሃድ ድርጅቶች መሠረቱ የሚታገሉለት ኅብረተተሰብ ነው እንዲሉ ፤ እኛ በመላው ክፍለ ዓለም ተበትነን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ትግላችን የጎለበተ ፣ ተከታታይነት ያለውና የተቀነባበረ እንዲሆን በዜግነታችን ጠቋሚ ሃሳባቱን ማቅረቡ ተገቢ መሆኑን አምነንበት ይህንን አመላካች የሆኑ ሃሳቦችን አፍቃሪ ሕዝብ ለሆኑ ድርጅቶች በሙሉ እናስተላልፋለን ።

**ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንዲሉ ፤ በጋራ ለመታገል እንነሳ !**

**ሕዝባችን የጀመረውን ትግል በድል እንደሚወጣ እሙን ነው !**